# <u>የፖለቲካ ሽሙጥ</u>

(ከአስተዋይ በቀለ)

## የእኛስ ነገር አይነሳ!

የእኛስ ነገር አይነሳ! እናውቃለን የሚለው በዛ፡፡ አንዱም አሳራጊ የፖለቲካ ካህን ሆነብን፡፡ እግዚአብሔር አይወደውም ዲክታተር አትበሉን አለን፡፡ ሰውየውን ፓትርያርክ አድርጎ መስቀል ሊያሳልመን ፈለገ፡፡

የጉድ እኮ ነው! የኛስ ነገር አይነሳ ! ሌላው ቅሌታሙ አሸርጋጅ ባላምባራስ ደግሞ፣ ከእናካቴው ማን እንደሱ ይግዛን- ይገዝግዘን እያለ የጌይ ዘፈኑን አስተጋባው፡፡ ቅሌት ገሃድ ሲወጣ እንዲህ እንደአሁኑ ታይቶ አይታወቅም፡፡

ዲያስፖራ ዓይኑን በጨው ስለታጠበ ነው መሰል ቢቀል ቢቀል አያፍርም፡፡ ሕዝቡ ሳአሊለነ ቅድስት ሲል፣ ዲያስፖራ ሰላሣ ስድስት እያለ ያደፈርሳል፡፡ ክተት ሲባል ይበትናል፡፡ ሕብረት ሲገነባ ይንዳል፡፡ ደህና ሰው ብቅ ሲል ያጠፋል፡፡ እግዚአብሔርን ትቶ ሞላጫ ያመልካል፡፡ ገንዘብ ይለምንና በጅሮዱን ይሰውራል፡፡ ሁሉን ነገር እንደ ሽሚዛ አድርቆት ቀረ እግዚአብሔር ይይለት፡፡

አስመራ ላይ ለጠላት ሎሌነት አድሮ በአስከርባ እየተረገጡ አርበኛ ነኝ ማለት ምን ይሉታል? በሌለ አውድማ ቼ- ነኝ ነፃ አውጪ ነኝ እያሉ ይፏልላሉ! ቅድስና ነው ወይስ መረገም፡፡ የጉድ እኮ ነው! ከተቃዋሚ ፖለቲከኛ ይልቅ በአንድ እግሩ ቆሞ ያስቀደሰ ተሻለ፡፡

የኛስ ነገር አይነሳ! እንደው መፏለል፣ እንደው መደናበር፣ መጋጨት፣ መበታተን፣ እርስ በርስ መጠፋፋት፡፡ እንደው ያቺን የፈጣሪ ቀን እንጠባበቅ እንጂ ፖለቲከኛስ የለንም፡፡ ዲሞክራሲ አልሰራም ነው ነገሩ፡፡

ዲያስፖራ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ጂ.ፒ.ኤሱ እኔ ነኝ ብሎ ሞላጫ ሰብስቦ ገደል ከተተን፡፡ የውስጡ አለኝታ አጥቶ እጁን ሰጠ፡፡ ዲሞክራሲ ወደ ሞቦክራሲ ተሸጋገረ፡፡ ዘራፊው አገሪቱን እየጋጠና እያማጋጠ ነው፡፡ መድረክ መንገድ ጠፍቶበት ግንባር ነኝ ብሎ እንደ ዶሮ ቆጥ ላይ ሰፍሮ በውስጡ ያለው ስብጥር ጤና ነስቶት ኩስ በዝቶበታል፡፡

ቀሪውም በምርጫው ዝርፊያ ተህድሶ ተክኖታል፡፡ ስብራት ያልገባው ደግሞ ተባበር ወይ ተሰባበር ይላል፡፡ እግዚአብሔር ጽንዕት በሆነች ኃይል አገራችንን ያድንልን እንጂ ተቃዋሚስ ሰኋል፡፡

ይህን ሁሉ ያመጣው ግንቦት ነው፡፡ የጉድ እኮ ነው፡፡ የኛስ ነገር አይነሳ! ያንዱ ግንቦት ሲገርመን ሌላው ደግሞ ግንቦት ብሎ ተነሣ፡፡ ግንቦት ወርሃዊ መርገም ነው፡፡ የግንቦት ብርሃን አይታመንም፡፡ ቀስ በቀስ ወደ ቀትር ተቀይሮ ያቃጥላል፡፡ ወዮልህ አበሻ ራስህ እንዳይነደል ተጠንቀቅ! አገርስ መቼም መከራዋን እያየች ነው ከግንቦት ብርሃን ጨለማ ተሽሎ ተገኘ፡፡ ፀጋ ነው፡፡ እረፍት ይሰጣል- ሰውነት ያድሳል ተገንም ነው ለማጥቃት፡፡

አበሻ አይገረምህ! ግንቦት ከግንቦት ጋር እደራደራለሁ አለ አሉ፡፡ ድሮስ “ዘመድ ከዘመዱ አህያ ካመዱ” አይደል የኛስ ነገር አይነሳ የጉድ እኮ ነው!

ይቀጥላል…..